5ኛ ዓመት ቁጥር 47
5th year No. 47

ባህር ዳር ሀምሌ 29 ቀን 1992 ዓ.ም.
Bahir Dar 5th Aug. 2000

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 3.40	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ 312 p.O.BOX

ማውጫ	Contents
አዋጅ ቁጥር 47/1992 የአማራ ብሄራዊ ክልል የአካባቢ ጥበቃ፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ገጽ 8	Proclamation No 47/2000 Enviromental protection, land Adminstration and Use Authority Establishment Proclamation Page 8

አዋጅ ቁጥር 47/1992
የአማራ ብሄራዊ ክልል የአካባቢ ጥበቃ፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

መሬት፣ውሃና አየር የመሳሰሉት የአካባቢያችን የፈተጥሮ ሀብቶች የሰው ልጅ ህልውና መሠረቶች በመሆናቸው በአያያዝና አጠቃቀም ጉድለት ሣቢያ የሚደርሰውን ብክለት በማስወገድ፣ የተፈጥሮ ሃብቱ ሚዛን እንደተጠበቀ ጥቅም ላይ እንዲውሉና ለመጪዎቹ ትውልዶች እንዲተላለፍ ማድረግ ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ፣

PROCLAMATION NO 47/2000
ENVIROMENTAL PROTECTION, LAND ADMINSTRATION AND USE AUTHORITY ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHERE AS, it is necessary to avoid enivromental pollution caused by the improper management and utilization of the environmental natural resources such as land, Water and air which are the basic human life determinants should be made by maintaining the ecological balance in view of passing them to future generations;

~~385~~ 381 ~~369~~ 382

የተፈጥሮ ሃብትን መሠረት በማድረግ የሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች በተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ማረጋገጥና ለዚህም የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት አተገባበራቸውን መከታተልና መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአካባቢ ደህንነት መብቶችን ፣ የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደርን ፣ ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት ልማትን አስመልክቶ በክልሉ ህገ መንግሥት መሠረት የወጣውን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ የሚያስፈጽም ራሱን የቻለ ህጋዊ አካል ማቋቋም በማስፈለጉ፣

በአማራ ብሄራዊ ክልል ህገ መንግሥት አንቀጽ 49/3/1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

WHERE AS, it is necessary to ensure that the development activities on the natural resource are conservation based, and to device and adopt a working mechanism to monitor and evaluate the implementation of these activities;

WHERE AS, it is necessary to establish an organ of juridical personality to implement the proclamation of the Amhara National Region Administration and use of rural Land on matters that concern environmental safety rights, land administration and use and sustainable development of natural resource.

NOW, THERE FORE, pursuant to article 49/3/1 of the Constitution of the Amhara National Region, it is here by proclaimed as follows

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአካባቢ ጥበቃ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 47/1992" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ

1. " አካባቢ " ማለት የተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ ሃብቶችና ቅርሶች እንዲሁም የእነዚህን ሃብቶች ጥራት፣ መጠንና የሰው ልጅ ደህንነትን የሚነኩ ውጫዊ ሁኔታዎች እና ተጽዕኖዎች ድምር ነው።

2. "የአካባቢ ጥበቃ" ማለት የሰው ልጅን ጨምሮ የማንኛውም አካል ሕይወትና እድገት የሚወስኑ የመሬት፣ የውሃና የአየር የመሳሰሉ ሌሎች የአካባቢ ሃብቶች ክስተቶችና ሁኔታዎች ጥበቃ ነው።

3. "መሬት" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ባለሥልጣኑ የሚያስተዳድረው የገጠር መሬት ነው።

4. "የመሬት አጠቃቀም" ማለት መሬት ሊሰጥ የሚገባቸውን ጥቅሞች አወሳሰንና ለመሬት የሚደረገውን አያያዝ ነው።

5. "የመሬት አስተዳደር" ማለት የይዞታና

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as " the Environmental protection, Land administration and use Authority Establishment proclamation No. 47/2000,"

2. Definition

Unless the Context other wise requires, in this proclamation,

1. "Environment" means the totality of all natural and human made resources and heritages as well as the external conditions and impacts, which affect their quality and quantity of said resources and welfare of human beings.

2. "Environmental protection" means the protection of land, water, air and similar other environmental resources, phenomenan and conditions which affect the life and development of all living organisms including human beings.

3. "Land" means the rural land that the Authority administer pursuant to this proclamation"

4. "Land use " means the decisions of alternative use of what the land is expected to give and the mechanism of land management .

5. " Land Administration" means the decisions of

362

367

ሌሎች የመሬት ተጠቃሚዎች መብቶች /ግዴታዎች/ አወሳሰን ነው::

6. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋመው የአማራ ብሔራዊ ክልል ነው::

7. "ባለሥልጣን" ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመ የአካባቢ ጥበቃ፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ባለሥልጣን ነው::

holdings and other land users rights or obligations.

6. "Region" means the Amhara National Region established pursuant to article 47 of the constitution of federal Democratic Republic of Ethiopia.

7. "Authority" means the Environmental protection, land administration and utilization Authority established pursuant to this proclamation.

ክፍል ሁለት

የባለስልጣኑ መቋቋም ተጠሪነትና ዓላማ

PART TWO

Establishment, Accountability And Objective of The Authority

3. የባለሥልጣኑ መቋቋምና ተጠሪነት

1. የአማራ ብሔራዊ ክልል የአካባቢ ጥበቃ፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ባለሥልጣን ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" እየተባለ የሚጠራ፣ ራሱን የቻለ እና ሕጋዊ የሰውነት መብት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

2. ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል::

3. Establishment And Accountability Of The Authority

1.The Environmental protection, Land administration and Utilization Authority here in after referred to as " the Authority" is here by established as an autonomous body having its juridical personality under this proclamation.

2. The Authority shall be accountable to the executive committee of the region and the presidant.

4. የባለሥልጣኑ ዓላማዎች

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል

1. በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ልማት እንቅስቃሴዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮች የሰውን ልጅ ደህንነት ለመንከባከብ፣ የአካባቢ የተፈጥሮ ሃብቶችን ዘላቂነት ባለው መንገድ ለመጠበቅ፣ ለማልማትና ለመጠቀም በሚያስችል ሁኔታ መካሄዳቸውን ማረጋገጥ፣

2. የክልሉን የገጠር መሬት በፌዴራልና በክልሉ ሕገ መንግሥቶች መሠረት በአግባቡ የሚያገለግሉትን፣ የሚተዳደርበትንና አጠቃቀሙ የሚወሰንበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

4. Objective Of The Authority

The Authority shall have the following objectives:

1. Ensure that matter's pertaining to the region's social and economic development activities are carried out in a manner that will protect the welfare of human beings as well as sustainable protect, develop and utilize the resources.

2. Create conducive atmosphere by which the management, administration and use of rural land of the region could be appropriately decided pursuant to federal & regional constitutions.

5. የባለሥልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት

1. የባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት በባህር ዳር ከተማ ይሆናል::

2 እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

5. Head Office Of The Authority

1. The head office of the Authority shall be in Bahir Dar.

2. As necessary it may have branch offices.

363

ይኖሩታል

ክፍል ሦስት

የባለስልጣኑ ድርጅታዊ አቋም፣ የቦርዱ አባላት፣ ጠቅላላ ስልጣንና ተግባር

6. ድርጅታዊ አቋም

ባለስልጣኑ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል::

1. አንድ የሥራ አመራር ቦርድ

2. በቦርዱ አቅራቢነት በክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሾም የባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ እና አንደአስፈላጊነቱ አንድ ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣

3. ሌሎች ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ይኖሩታል::

7. የቦርዱ አባላት

ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል:: ቁጥራቸው እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል::

8. የቦርዱ ጠቅላላ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

1. የክልሉን የአካባቢ ጥበቃ፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም በሚመለከቱ በጥናትና ምርምር ላይ የተደገፉ ልዩ ልዩ የፖሊሲ፣ የስልትና የሕግ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የውሣኔ ሃሣብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል::

2. ባለሥልጣኑ የሚያዘጋጃቸውን የአካባቢ ደረጃዎች፣ የቴክኒክ መመሪያዎችና የድርጊት መርሃ ግብሮች ይመረምራል፣ ያፀድቃል::

3. የባለሥልጣኑን የመዋቅራዊ አደረጃጀት ረቂቅ መርምሮ ከውሣኔ አስተያየት ጋር ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ያፀድቃል::

4. በክልሉ ውስጥ የአካባቢ ጉዳይን በተመለከተ

PART THREE

Organizational Structure Of The Members Authority Powers And Duties Of The Board

6. Organizational Structure

The Authority may constitute:

1. A managing Board

2. A manager and as necessary a deputy manager to be assigned by the executive committee of the region up on the presentation of the board.

3. Other necessary responsible personnels and employees.

7. Members of The Board

The Board in addition to the chairman shall have members to be assigned by the executive committee of the region. The numbers may be decided as necessary.

8. General Powers And Duties Of The Board

The Board shall have the following powers and Duties to:

1. Discus on policy, strategy and law issues supported with study and research concerning environmental protection, land administration and use of the region. Submit decision proposal to the executive committee and upon approval and follow up the implementation;

2. Inspect and approve environmental standards, technical directives and action plans prepared by the Authority;

3. Scrutinize the draft organizational structure of the authority and submit to the executive committee with its proposal for approval;

4. Establish coordinating committee that assist the

በየደረጃው ባለስልጣኑን የሚያግዙ አስተባባሪ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ተግባርና ኃላፊነታቸውን ይወስናል።

Authority concerning environmental issues at various level in the region; decide their duties & responsibilities;

5. በማኅበረሰብ ደረጃ የተሰባሰቡና አካባቢን አጀንዳቸው ያደረጉ ማኅበራት ድጋፍ የሚያገኙበትንና ውጤታቸው የሚገመገምበት ስልት እንዲዘጋጅ ያደርጋል። አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፣

5. Cause the preparation of strategies where by associations at the community level that have environmental concern get assistances and their result be evaluated. Follow up their implementations;

6. የባለሥልጣኑን የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድና በጀት በመመርመር ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል።

6.Scruthnize and submit short, medium and long term plan and budget of the authority to the executive committee and follow up its implementation upon approval;

7. ሥልጣንና ተግባሩን ለመወጣት እንደአስፈላጊነቱ አጥኚ ቡድኖችን ይሰይማል፣

7. Assign study teams as may be necessary to accomplish its powers & dueities;

8. የባለሥልጣኑን ሥራ አስኪያጅ፣ ም/ሥራ አስኪያጅና ሌሎችንም የሥራ ኃላፊዎች እንደአስፈላጊነቱ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በማቅረብ ያሾማል።

8.Present the manager, duety manager and other heads of the authority as necessary to the regional executive committee.

9. የስብሰባና የውሣኔ አሰጣጥ ስነ ስርዓት

9. Meeting & Decision Procedure

1. ቦርዱ መደበኛ ስብሰባውን በሦስት ወር አንድ ጊዜ ያደርጋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

1. The board shall convene its regular meeting once in every three months; however, extra ordinary meetings shall be held at any time, as may be necessary.

2. ከቦርዱ አባላት አብዛኛዎቹ በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

2.The presence of the majority members of the board shall constitute a quorum.

3. የቦርዱ ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምጽ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

3.Decissions of the board shall be passed by simple majority vote. However in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

4. የዚህ አንቀጽ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

4.With out prejudice to the other provisions of this article the board shall adopt its own rules and meeting procedures.

ክፍል አራት

የባለስልጣኑ እና የሥራ አስኪያጆች ጠቅላላ ስልጣንና ተግባር

PART FOUR

General Powers & Duties Of The Authority & Managers

10. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

10. Powers& Duties Of The Authority

The Authority shall have the following powers and duties to:

1. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልሉን የመሬት ዓይነትና መጠን አጥንቶና

1. Study and register the type & size of the land of the region; administer and follow up the use;

365 ~~365~~ ~~329~~

365

መዝግቦ ይይዛል፣ ያስተዳድራል፣ አጠቃቀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ውጤታማነቱን ይገመግማል፣

control & evaluate its effectiveness in co-ordination with the concerned organs.

2. መሬት በተለያዩ ምክንያቶች ምርታማነቱን እንዳያጣና ከጥቅም ውጭ እንዳይሆን የመሬት ተጠቃሚዎች በይዞታቸው ላይ የተለያዩ እንክብካቤዎች እንዲያደርጉ ትምህርት ይሰጣል፣ የማትጊያ ዘዴዎችን ይቀይሳል፣ ግዴታቸውን በማይወጡ ላይ እርምጃ ይወስዳል።

2. Educate, device sensitization mechanisms so as to enable land users to protect the land from further production deterioration and take appropriate punitive measures against those failing meeting their obligations.

3. የክልሉን መሬት እያጠና አጠቃቀሙን ይወስናል። እንደአስፈላጊነቱም መረጃውን ለተጠቃሚዎች ይሰጣል፣

3. Study land of the region's and determine land use if necessasary deciminate this information to users.

4. ቀለል ያለ ቅየሳ በመጠቀም ለእያንዳንዱ የመሬት ባለይዞታ የይዞታውን ልክና አዋሳኝ የሚያሳይ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ካርታና ደብተር ይሰጣል።

4. Conduct simple cadastral survey and issue map and a book of certificate to each land holder with a mention of the plot size and its adjacent boarder's.

5. በመሬት የመጠቀም መብት የተሰጣቸው ግለሰቦች /ድርጅቶች/ የያዙትን መሬት የመጠቀም መብት በውርስ /በኪራይ የሚያስተላልፉበትን እና ሌሎች መሬትን ለማስተዳደር የሚወጡ መመሪያዎችንና ደንቦችን ያስፈጽማል።

5. Cause the execution of directives or regulations issued for transferring the right to use land possessed by individuals or organizations through heirs or lease and other land admistration directives or regulations.

6. የግል ባለሃብቶች በመሬት ላይ የልማት ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የአጠቃቀም እቅዳቸውን እየገመገመ ያፀድቃል፣

6. Evaluate and approve the use plans of private investors prior to their start of development activity on land.

7. በፌዴራል የአካባቢ ፖሊሲ ላይ ተመስርቶ የክልሉን የአካባቢ ስልቶችና ሕግጋት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

7. Prepare proposals of environmental strategies and laws of the region based on the federal environmental policy And implement upon approval.

8. የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን ይዘረጋል አፈጻጸማቸውን ይከታተላል። ይቆጣጠራል።

8. Developed systems that enable to evaluate environmental impact assessment and follow up & monitor the implementation.

9. በረሃማነትን ለመከላከልና የተጐሳቆሉ ወይም የተራቆቱ አካባቢዎችን ስርዓተ ምህዳር መልሶ ለማገገም የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ የማስፈጸሚያ ስልቶችን ይዘረጋል፣

9. Carry out studies and adopt implementing strategies for the rehabilitation of degraded ecological areas and fight against desertification.

10. የክልሉ ብዝሃ ሕይወት ሃብት ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶች፣ ፓርኮች፣ አጠቃቀምና አያያዝን የሚመለከቱ ጥናቶች ያካሂዳል። ስልቶችን፣ ሕጐችንና ደንቦችን ያዘጋጃል። ሲፈቀድም በሚመለከታቸው አካላት በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል። አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

10. Study the use and management of the regional biodiversity of resources, natural and man made heritages and parks. Prepare strategies and regulations. Assist and monitor their implementation by concerned organs once they are approved.

366

366

~~370~~

11. በክልሉ ውስጥ ማህበረሰቦች በተሻለ ሁኔታ አካባቢያቸውን ለመጠበቅ እንዲችሉ ትምህርት ይሰጣል፣ ልዩ ልዩ የማበረታቻና የቁጥጥር ዘዴዎችን እየቀየሰ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ጠቀሚታ ያላቸውን ልምዶችና አሰራሮች ያሰራጫል::

11. Educate the communities so that they protect their environment in better conditions. Design and implement incentives and regulatory methods; disseminate useful experiences and skills.

12. በሕግ የተደነገጉ የፌዴራሉ የአካባቢ ደረጃዎች ሳይጣሱ የክልሉን የአካባቢ ደረጃዎች ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም አግባብ ባላቸው አካላት በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል::

12. Prepare environmental standards of the region in line with the federal environmental level; ensure its applications by the appropriate bodies up on approval.

13. በክልሉ በየትኛውም ቦታ ላይ ያለን ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝ፣ መልሶ መጠቀም እና አወጋገድ የሰውን ጤና የአካባቢን ደህንነት በማያቃውስ ሁኔታ መፈጸሙን ያረጋግጣል፣ ለዚሁም ተገቢ መመሪያዎችን በማውጣት በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል።

13. Make sure of the collection management recycling and disposal of waste and waste management to assure the protection of individuals and environmental health. Also, issue relevant directives to this effect and follow up their implimentation.

14. የክልሉን የአካባቢ፣ የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር መረጃዎች ለማደራጀት ስርዓት ይዘረጋል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ትንተና እያካሄደ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል::

14. Establish a system to organize adate base for enivironment land administration and use of the region and collect, analyze and disseminate information to the users.

15. የክልሉን የአካባቢ፣ የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደርን የሚመለከቱ ወቅታዊ ዘገባዎችን ለቦርዱና ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣

15. Submit timely reports of the regional environmental protection, land administration and use conditions to the board and the regional executive committee.

16. በክልሉ አካባቢን፣ የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደርን በሚመለከቱ ጉዳዮች አግባብ ላላቸው አካላት ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣

16. Render advice & technical support on matters concerning environment, use and administration of land in the region to the appropriate bodies.

17. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል::

17. Own property, enter in to contract, sue and be sued in its own name.

18. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል::

18. Perform such other activities necessary to execute its objective.

11. የባለሥልጣኑ መ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

11. Powers and Duties of the Managers

1. ሥራ አስኪያጁ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል

1. The manager shall have the following powers and duties to:

1.1. የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

1.1. Being the main executive body, direct and administer the activities of the authority.

1.2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1.1 አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ አስኪያጁ

1.2. With out prejudice to the general provisions of sub article 1.1 of this article, the manager shall

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 የተመለከተውን የባለሥልጣኑን መ/ቤት ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል፣

a. Apply into effect the power and duty of the authority provided under article 10 of this proclamation.

ለ. በሰቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

b. Employ, administer and dismiss its employees in accordance with the civil service law.

ሐ. የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

c. Prepare action plan and budget of the authority and implement the same upon approval.

መ. ባለሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

d. Effect expenditure in accordance with the approved budget and plan of action of the authority.

ሠ. ባለሥልጣኑ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፣

e. Represent the authority in its dealings with other third parties

ረ. የባለሥልጣኑን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ወቅታዊ ዘገባ ለቦርዱና ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ያቀርባል፣

f. Submit to the board and the regional executive committee timely activity reports of the authority.

2. ም/ሥራ አስኪያጁ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

2. The Deputy manager shall have the following powers and duties to

ሀ. በዋና ሥራ አስኪያጁ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል::

a. Carry out tasks which shall be specifically entrusted to him by the general manager

ለ. ዋናው ሥራ አስኪያጅ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ እርሱን ተተክቶ ይሠራል::

b. Represent the General manager in his absence or unable to do his task.

ክፍል አምስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

PART FIVE
Miscellaneous provisions

12. በጀት

12. Budget

የባለሥልጣኑ በጀት ከሚከተሉት የፋይናንስ ምንጮች የሚመደብ ይሆናል::

1. በክልሉ መንግሥት ከሚመደብ በጀት
2. ከብድርና ከእርዳታ
3. ከሌሎች

The budget of the authority shall be drawn from:

1. The budget allocated by the regional state
2. Loan and donation
3. Other sources

13. የሂሣብ መዛግብት

13. Books of accounts

1. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል::

1. The Authority shall keep appropriate and complete books of accounts.

2. የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ የኦዲት መ/ቤት በየዓመቱ ይመረመራሉ::

2. The books of accounts and financial documents of the authority shall be audited every year by the auditor general

14. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

14 Power to issue directives

ባለስልጣኑ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን አለው::

The authority shall have power to issue directives necessary to execute this proclamation

15. የመተባበር ግዴታ

15. Duty to cooperate

ማንኛውም ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ለዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚወጡት መመሪያዎች አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት::

Any person or juridical personality has an obligation to cooperate for the execution of this proclamation or directives issued pursuant to this proclamation.

16. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ
ይህ አዋጅ በዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀመሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር
ሐምሌ 29 ቀን 1992 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

16. Effective Date.
This proclamation shall come into force in the date of its publication in the Zikre Hig Gazzette.

Done at Bahir Dar
This 5th day of August 2000
The Council of The Amhara National Regional State.

369

369

~~277~~